የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ
NATIONAL BANK OF ETHIOPIA
ADDIS ABABA

የካቲት 27 ቀን 2013 ዓ.ም.

# በትግራይ ክልል አሮጌ ብር መቀየርን በተመለከተ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተሰጠ ማሳሰቢያ

እንደሚታወቀው ከትግራይ ክልል በስተቀር በመላ ሀገሪቱ አሮጌዉን ብር በአዲስ የመቀየሩ ሥራ በተሳካ ሁኔታ ተጠናቋል፡፡ በነበረዉ የሕግ ማስከበር እንቅስቃሴ ሳቢያ ብር የመቀየሩ ሂደት ተስተጓጉሎ እንደነበር የሚታወስ ሲሆን ይህንኑ ታሳቢ በማድረግ ከ100ሺ ብር በታች አሮጌ ብር ያላቸዉ እንዲቀይሩ የ14 ቀናት ተጨማሪ ጊዜ መፈቀዱ ይታወሳል፡፡

እስካሁን ባለዉ በክልሉ ይቀየራል ተብሎ የሚታሰበዉ አሮጌ የገንዘብ መጠን በአብዛኛዉ የተቀየረ በመሆኑና የሚቀየረዉ አሮጌ ገንዘብ መጠንም በጣም ጥቂት መሆኑን ታሳቢ በማድረግ በክልሉ የተጀመረዉን ብር የመቀየር ሥራ ለማጠናቀቅ የጊዜ ገደብ ማስቀመጡ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በዚህ መሠረት ከየካቲት 29 እስከ መጋቢት 10 ቀን 2013 ዓ/ም ባሉ ተጨማሪ ቀናት አሮጌዉ ብር ሙሉ በሙሉ እንዲቀየር፣ ይህ ማሳሰቢያ የመጨረሻ መሆኑ ታዉቆ የባንክ ቅርንጫፍ በተከፈተባቸዉ በሁሉም የክልሉ አካባቢዎች በመሄድ ይኸዉ ተግባራዊ እንዲደረግ፣ ባንኮችም በዚሁ መሠረት ተግባራዊ እንዲያደርጉ ከአደራ ጭምር እናሳስባለን፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ